በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽ/ቤት
የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት/2015

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽ/ቤት
የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽ/ቤት የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽ/ቤት ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የዋና ኦዲተሮች የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽ/ቤት ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች ፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በፍርድ ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የተጠቃለለ የሂሳብ ማመዛዘኛ፣

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣</u>

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽ/ቤት የ2014 የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

<u>ወጪ፤</u>

1. የከፍተኛ መንግስት ኃላፊዎችን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ አንቀፅ 2 “ 4/ ስር ለከፍተኛ የመንግስት ኃላፊ መንግስት የመኖሪያ ቤት ማቅረብ ካልቻለ ኃላፊው ቤት እስኪሰጠው ድረስ በመስሪያ ቤቱ በጀት ተይዞለት የሚከፈል በየወሩ አስራ ስምንት ሺ ብር 18,000.00 የቤት ኪራይ አበል ይከፈለዋል ይላል፡፡ በመሆኑም በምክር ቤቱ የሚገኙ ኃላፊዎች ክፍያ የተፈጸመላቸው በዚህ አግባብ ስለመሆኑ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የምክር ቤቱ ምክትል አፈ-ጉባኤ ለሆኑት ከየካቲት 1/2014 ዓ.ም ጀምሮ በወር 14,970.00 ለመክፈል ጽ/ቤቱ ከፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ጋር ውል የፈጸመና የካቲት እስከ ግንቦት ወር በጠቅላላ ብር 59,880.00 ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም ለምክትል አፈ ጉባኤ በተጨማሪም የቤት አበል ብር በወር 18,000.00 የአራት ወር ብር 72,000.00 በደመወዛቸው ላይ ተጨምሮ ያለአግባብ የተከፈለ መሆኑ በኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
2. የከፍተኛ መንግስት ኃላፊዎችን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ አንቀፅ 2 “ 1/ ስር “ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊ” ማለት የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሚኒስትር፣ ሚኒስትር ዴኤታ፣ ጠቅላይ ዓቃቢ ሕግና ምክትል ጠቅላይ ዓቃቢ ሕግ፣ የፌደራል መንግስት ተቋማት ኮሚሽነር፣ ምክትል ኮሚሽነር፣ ዋና ዳይሬክተር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተር ፣ የሕዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤና ምክትል አፈ-ጉባኤ፣እንደዚሁም በነዚህ ደረጃ የተሾሙ የበላይ ኃላፊዎች መሆናቸውን፣እንዲሁም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባልና የጽ/ቤት ሃላፊ የደንብ ልብስ እና በቋሚነት የተመደቡ የቋሚ ኮሚቴ ፀሐፊዎች የመኖሪያ ቤት ዳረጎት ለመወሰንና አንቀጽ 3 ለማሻሻል በቀን 02/1/2012 ዓ.ም በወጣ መመሪያ መሰረት በቋሚነት ለተመደበ የቋሚ ኮሚቴ ጸሐፊ የመኖሪያ ቤት ዳረጎት በየወሩ ብር 3,787.35 እንዲከፈላቸው በተላለፈው መመሪያ መሰረት ክፍያ ስለመፈጸሙ ለማረጋገጥ ኦዲት

ሲደረግ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባልና የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ፀሐፊዎች ለሆኑት መኖሪያ ቤት ባለመሰጠቱ (ባለማግኘታቸው) በሚል ከህዳር 7/2014 እስከ ታህሳስ 21/2014 በማዶ ሆቴል እንዲያርፉ የተደረገና ለሆቴሉ አገልግሎት በድምሩ ብር 240,220.32 የተከፈለላቸው ቢሆንም የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባልና የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ፀሐፊዎች ለሆኑት የተከፈለ ቢሆንም ከሆቴል ክፍያ በተጨማሪ የመኖሪያ ቤት አበል የህዳር ወር እና የታህሳስ ወር በድምሩ ብር **36,000.00**(18000*2) ተከፍሏቸው መገኘቱ በኦዲት ታውቋል፡፡

3. የመንግስት ሠራተኞች የቀን ዉሎ አበል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 3/2012 በተጨማሪ በቁጥር፡- ፐ.ስ.ሚ ጠ30/ጠ13/1052 በቀን የካቲት 01/2008 ዓ.ም የቀድሞ የፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስትር የመንግስት ተሿሚዎችና ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል ለማሻሻል በወጣው መመሪያ ቁጥር 5 እና 6 ስር በተቀመጠው የበላይ ሀላፊዎች ጋር የሚንቀሳቀሱ ጥበቃዎች እና ሾፌሮች በደመወዛቸው መጠን የቀን የምግብ አበል በገንዘብ እንዲሰጣቸውና የመኝታ ወጪያቸው ግን ሀላፊው ባረፈበት ሆቴል ወይም በቅርብ በሚገኝ ሌላ ሆቴል የባለአንድ አልጋ ክፍል ወጪ በሚያቀርቡት ደረሰኝ መሠረት እንዲሸፈን በተገለጸው መሰረት መመሪያው ተግባራዊ ስለመደረጉ በተወሰደ የኦዲት ናሙና አንድ የመስሪያ ቤቱ ሹፌር ጎንደር ለስራ ጉዳይ ከበላይ ሀላፊ ጋር በሄዱበት ጊዜ ለቆዩበት ቀናቶች ለአደሩበት የአልጋ 40% ተቀንሶ ብር 120,036.60 መከፈል ሲገባው በወጪ ማስመሰከሪያ ቁጥር 16974 በሂሳብ መደብ 2221101 ብር 125,007.00 በመከፈሉ ብር 4,970.40 በብልጫ የተከፈለ መሆኑ እንዲሁም አራት ከአማራ ክልል ለስብሰባ ከበላይ ሀላፊ ጋር ወደ አዲስ አበባ የመጡ ሹፌርና ጥበቃዎች ለቆዩበት ቀናቶች የአደሩበት የአልጋ ደረሰኝ በወጪ ማስመሰከሪያ ቁጥር 16691 በሂሳብ መደብ 2221101 ብር 38,183.88 ያወራረዱ ቢሆንም ከአገኙት የውሎ አበል የአልጋ 40% ተቀንሶ ብር 34,669.48 በመከፈሉ ብር 3,514.40 በብልጫ የተከፈለ መሆኑን በጠቅላላ በድምሩ ብር 8,484.8 ያለአግባብ የውሎ አበል ክፍያ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑን በኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

4. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 ስለፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ክፍል 3 የመንግስት ገንዘብ ክፍያ አንቀጽ 12 ክፍያ እና ወጪ የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ሊፈፀም ወይም ወጪ ሊደረግ

የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ ነው ይላል፡፡ በመሆኑም በፌዴሬሽኑ የወጡ ወጪዎች በጀት አመቱን የጠበቁ ለመሆናቸው ኦዲት ሲደረግ በቀን 29/9/2014 በወጪ ማስመስከሪያ 18856 በሂሳብ መደብ 2231107 ለኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ከ2011-2012 ለተከናወነ ስራ በበጀት ዓመታቸው መከፈል ሲኖርበት በጠቅላላ ብር 154,581.53 በ2014 በጀት ዓመት ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

5. በጽ/ቤቱ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት የተገዛው ዕቃ ወደ መ/ቤቱ ዕቃ መጋዘን ለመግባቱ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ የቀረበለት መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፤ በሂሳብ መደብ 2211107(6217) በተለያዩ የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር እና ቀኖች በድምሩ ብር 2,200,655.10 የነዳጅ ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም ነዳጅ ስለመግባቱ ሞዴል 19 ለኦዲቱ ባለመቅረቡ የክፍያውን አግባብነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

. **ተሰብሳቢ**

6. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ፤ በመመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። ይሁንና መ/ቤቱ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን በደንቡና በመመሪያው መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ የሚያደርግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኢዲት ሲደረግ በበጀት ዓመቱ በሪፖርት ከሚታይ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ በሂሳብ መደብ 5217301 ብር 398,201.17 ሂሳቡ ከማንና መቼ እንደሚሰበሰብ የማይታወቅ(ማስረጃ የሌለው መሆኑ) በተንጠልጣይ ሂሳብ የተመዘገበና መቼ እንደተያዘ የማይታወቅ መሆኑ፤

7. በፌዴራል መንግስት መስረያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለትአንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 5 በተመለከተው መሰረት ተከፋይ ሂሳቦችን ለመከታተል ተገቢው የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱንና መሥሪያ ቤቱ ተከፋይ ሂሣቦችን በገባው ግዴታ መሰረት በወቅቱ የሚከፍል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ከሚታየው ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ ውስጥ፡-

- በሂሳብ መደብ 6172202 /5002/ ለተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የሚከፈል በድምሩ ብር 258,540.61 የተያዘ ሲሆን ሂሳቡ በተከፋይ መቼ እንደተያዘ ያልተገለፀ በመሆኑ የእርጅና ዘመኑን ማወቅ ያልተቻለ መሆኑ፣
- በሂሳብ መደብ 61725101/5061/ የማስያገዢያ ሂሳብ ብር 477,264.03 ከሁለት አመት በላይ የተያዘና የድርጅት ስሙ ያልተገለፀ በመሆኑ ለማን እንደሚከፍል የማይታወቅ መሆኑ፡በድምሩ ብር 735,804.64 መኖሩ በኦዲት ታውቋል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 7 ከተገለፁት በስተቀር የመ/ ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀም በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ፡፡

ህጋዊነትን ያልተከተሉ ጉዳዮች (Compliance Matters)

8. ህዳር 1999 የወጣው የፌዴራል ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች የውጭ አገር ነፃ ህክምና መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 5.1 መሰረት የአገር ውስጥና የወጭ አገር ህክምን እንዲያገኙ የተፈቀደላቸው የመንግስት ሀላፊዎች ከደመወዛቸው 2 % እንዲሁም የሀገር ውስጥ ህክምና ብቻ እንዲያገኙ የተፈቀደላቸው ኃላፊዎች በየወሩ ከደመወዛቸው 1% መዋጮ መክፈል አለባቸው ይላል ፡፡ ይሁን እንጂ ፌዴሬሽን ምክር ቤቱ በመመሪያው መሰረት እየሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከደመወዛቸው ላይ የህክምና መዋጮ በመመሪያው መሰረት ባለመቀነሱ በድምሩ ብር 13,104.00 ሳይሰበሰብ እንደቀረ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡
9. የፌዴራል መንግሥት የግዢ እና ንበረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 51 ንኡስ አንቀጽ 1/ሀ የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚችሉት እቃው ወይም አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ እጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ ነው ይላል፡፡ይሁን እንጂ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽ/ቤቱ በተለያዩ ጊዜያት በድምሩ ብር 2,035,146.87 ምንም አይነት ውድድር ሳይደረግ በቀጥታ ግዥ የተፈፀመ መሆኑን በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

10. ተሰብሳቢ

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ፣ በመመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። ይሁንና መ/ቤቱ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን በደንቡና በመመሪያው መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ የሚያደርግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በበጀት ዓመቱ በሪፖርት ከሚታይ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ፡-

- በሂሳብ መደብ 5217205 ብር 556,726.17 ከአንድ አመት በላይ በተሰብሳቢ ተመዝግቦ የሚታይ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 5217205 /በተለያዩ ጊዜ ከ2008 በጀት አመት ጀምሮ አምስትና ከአምስት አመት በላይ የተያዘ ለአቅራቢዎች የተከፈለ በድምሩ ብር 482,391.39
- በሂሳብ መደብ 5217313 ብር 3,327.81 ሳይሰበሰብ ከአምስት አመት በላይ የቆየ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 5217301 ብር 398,201.17 በተንጠልጣይ ሂሳብ የተመዘገበና መቼ እንደተያዘ የማይታወቅ በጠቅላላ ድምር ብር 1,042,445.37 በተሰብሳቢ ተይዞ የሚታይ መሆኑ ታውቋል፡፡፡

11. ተከፋይ ሂሳብ

በፌዴራል መንግስት መስረያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለትአንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 5 በተመለከተው መሰረት ተከፋይ ሂሳቦችን ለመከታተል ተገቢው የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱንና መሥሪያ ቤቱ ተከፋይ ሂሣቦችን በገባው ግዴታ መሰረት በወቅቱ የሚከፍል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ከሚታየው ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ ውስጥ፡-

- በሂሳብ መደብ 6172101 /5003/ ከአንድ አመት በላይ ብር 87,483.40 በተከፋይ የሚታይ ሂሳብ መሆኑ፤

➢ በሂሳብ መደብ 6172105/5006/ ከአንድ አመት በላይ በተከፋይ የተያዘ ዊዝሆልዲንግ ታክስ ብር 39,361.95 መሆኑ፣

➢ በሂሳብ መደብ 6172108 / 5009/ የሕክምና መዋጮ ከአንድ አመት በላይ በተከፋይ የተያዘ ብር 2,030.15 መሆኑ፣

➢ በሂሳብ መደብ 6172110 /5005/ ሌሎች የደመወዝ ተቀናናሾች ለአንድ አመት ብር 13,687.18 በተከፋይ ተይዞ የሚገኝ መሆኑ፣

በድምሩ ብር 55,079.28 ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ በኦዲት ታውቋል፡፡

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች(Emphasis matter)

12. **በጀት**

በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 3 አንቀጽ 12 መሠረት መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ በሥራ ላይ ሊያውሉ እንደሚገባቸው ይገልፃል፡፡ ሆኖም የጽ/ቤቱ በ2014 በጀት ዓመት ለሂሳብ መደብ የተመደበው የመደበኛ በጀት በአግባቡ ስራ ላይ ከዋለው ሂሳብ ጋር ሲነጻጸር አንዳንድ የወጪ አርዕስቶች ከ10% በላይ በጠቅላላ ብር 6,321,141.24 ያልተሰራበት በጀት መኖሩ ታውቋል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች(Other matter)

የንብረት አያያዝና አጠባበቅ በተመለከተ

13. የመ/ቤቱ የንብረት አስተዳደር እና አጠባበቅ በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 5 የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ ፣የመጠቀም ፣የመቆጣጠር እና አገልገሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንዳለባቸው ያዛል። በዚህ መሰረት ማዕከሉ የንብረት አመዘጋገብ እና አያያዝ በንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በግምጃ ቤት ውስጥ ላሉ ንብረቶች ቢን ካርድ እና ስቶክ ካርድ የማይጠቀሙ መሆኑ፤
- የቋሚ እና አላቂ እቃዎች በአንድ ክፍል ውስጥ ተቀላቅለው የተቀመጡ መሆኑ፤
- አስራ አንድ ካርቶን አዳዲስ የመኪና መለዋወጫ እቃዎች ያለ አገልግሎት የተቀመጡና መቼ እንደገቡ በቢን ካርድ ላይ ያልተመዘገቡ በመሆናቸው ጊዜያቸው የማይታወቅ መሆኑ፤
- ያገለገሉ ሶስት ፍላት ቴሌቭዥን 3 ዲኮደር 5 ሪሞት እና ሁለት የድሮ ቴሌቭዥን መስራት አለመስራታቸው በባለሙያ ሳይረጋገጡ በንብረት ክፍል ውስጥ ተቀላቅለው የተቀመጡ መሆኑ፡
- ከንብረት ክፍል ወጪ ተደርጎ ነገር ግን በአደራ ተብሎ ግምጃ ቤት የተቀመጠ ብዛት 8 የመኪና መለዋወጫ የተቀመጠ መሆኑ፤
- አገልግሎት የማይሰጡ ሶስት ዲስክ ቶፕ ኮምፒውተር ፡አንድ ጂፓስ ቴፕ ከነ እስፒከር አንድ ባለሁለት እስፒከር ሶኒ ቴፕ በግምጃ ቤት መስራት አለመስራታቸው በባለሙያ ሳይረጋገጡ በንብረት
- ሁለት የማይሰራ የስልክ ቀፎዎች በባለፈው ኦዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፡
- የሚወገዱ 24 የመኪና ጐማዎች እና በቁጥር አምስት አዲስ የመኪና ጐማዎች በአንድ ላይ የተቀመጡ መሆኑ፡
- ሶስት ጉርድ ጫማና አንድ የወንድ ቡስትና ጉርድ ጫማ አምስት መጫወቻ ኳሶች አገልግሎት የማይሰጥ የሁሃ ማጣሪያ በአንድ ላይ የተቀመጡ መሆኑ፡
- የሚወገዱ የመኪና መለዋወጫዎች እና ብረታ ብረቶች የተቀመጡ መሆኑ፤
- ወጪ የሆኑ ለኃላፊዎችና ለሹፌሮች የተሰጡ መኪኖች በሠራተኞች እጅ የሚገኙ ቋሚ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ (በዩዘር) ካርድ ላይ የማይመዘገቡ መሆኑ፤
- ለሰራተኞች የሚሰጡ የመፀዳጃ ሶፍት ብዛት 1092 በክፍሉ ውስጥ የሚገኝ መሆኑ፡

<u>የውስጥ ኦዲት በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ሪፖርት አለማድረግ በተመለከተ</u>

14. የፌዴራል መንግስት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 ክፍል 5 የውስጥ ኦዲት ዕቅድና ሪፖርት ማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳ ላይ በንዑስ አንቀፅ 3 በኦዲት ዕቅድ መሰረት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት እስከ ጥቅምት 30፣ የሁለተኛው ሩብ ዓመት እስከ ጥር 30

የሶስተኛው ሩብ አመት እስከ ሚያዚያ 30፣ የአራተኛ ሩብ ዓመት እስከ ነሀሴ 15 ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ እንደሚገባ ይገልፃል፡፡ በመሆኑም ጽ/ቤቱ 1ኛ ሩብ አመት ሪፖርት የተደረገው ግንቦት 15/2014 ዓ.ም ሲሆን ለስምንት ወር ከ15 ቀን የዘገየ መሆኑ፣ የሁለተኛ ሩብ አመት እና የ3ኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት የተደረገው መስከረም 6/2015 ዓ.ም ሲሆን ለአራት ወር ከ6 ቀን የዘገየ መሆኑ፣ የ4ኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት እስከ አሁን ደረስ ያልተደረገ መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

<u>የነዳጅ አጠቃቀም ሪፖርት በየወሩ የማይሰራና ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ</u>

15. የፌዴራል መንግሥት ተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል ሶስት አንቀጽ 9 የመንግስት ተሽከርካሪዎች ነዳጅ፡ ቅባትና ዘይት አጠቃቀምና ቁጥጥርን በተመለከተ በቁጥር 2 ላይ ለበላይ ኃላፊዎች እና ለኃላፊዎች ከሚመደቡ ተሽከርካሪዎች በስተቀር እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀው የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ.ሜትር መጠን ጋር እየተመዘገበ ተገቢውን ሪፖርት በየወሩ መቅረብ ይኖርበታል ይላል ጽ/ቤቱ በመመሪያውም መሰረት ነዳጅ አጠቃቀምን ተሽከርካሪዎች በሊትር የሚጓዙት ርቀት /normalization/ እየተመዘገበ ሪፖርት በየወሩ የሚደርግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የነዳጅ ስራው እየተሰራ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ክትትል ኦዲት፤</u>

16. የፌዴራል ዋና ኦዲተር የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ የተወሰደባቸውና ያልተወሰደባቸው ግኝቶች ሁኔታ ሲጣራ፡

እርምጃ ሊወሰድበት ከሚገባው አጠቃላይ የገንዘብ መጠን ውስጥ 22% እርምጃ እንዲወሰድበት የተደረገ ሲሆን በቁጥር ደረጃ ከተገለጹት የአሰራር ክፍተቶች ውስጥ ደግሞ 50% ማስተካከያ የተደረገባቸው ሲሆን 50% ማስተካከያ አልተደረገባቸውም። እርምጃ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል። ይኸውም፡-

1. ከውሎ አበል ተመላሽ ያልተደረገ በድምሩ ብር 16,066.00

2. ዕቃዎች በቢን ካርድ ላይ የማይመዘገቡ ወይም በእቃዎቹ ላይ የማይንጠለጠል ከመሆኑ በተጨማሪ የማቀናነስ ሥራ ያልተከናወነ መሆኑ፤እንዲሁም የሚሰሩና የማይሰሩ ንብረቶች በአንድ ላይ በንብረት ክፍል ውስጥ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

ከሰላምታ ጋር

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት